# SHORT COMMUNICATION

Ethiopian Journal of Behavioral Studies, 2021, 4 (2), 133– 142

# የትምህርትን ጥራት ለማረጋገጥ መከፈል የሚገባዉ ዋጋ ምን ያህል ይሆን? በእርግጥ ፈቃደኞች ነን የቱንም ያህል ዉድ ዋጋ ለመክፈል?

**አካለ ወልድ እሸቴ** *

## መግቢያ

ለዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ያነሳሳኝ በዋናነት በቅርብ ለመንግስት ባለስልጣኖች ለዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ና ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ለውይይትና ማሻሻያ ሃሳብ ለማሰባሰብ የቀረበው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናት ላይ ከትምህርት ጥራት አንፃር የተወሰኑ ሃሳቦችን በመሰንዘር ሌሎች ከእኔ የተሻለ ልምድና እውቀቱ ያላቸው ሰዎችን ወደማህበራዊ ውይይት እና ፅብረቃ እንዲመጡ ለማነሳሳት ነው። ፈረንጆቹ «ብረቱን መምታት ገና ሞቆ ሳለ ነው» እንደሚሉት ይህ መሠረታዊ የሆነ ጥናት ወደ ተግባር ከመለወጡ በፊት መሻሻል የሚገባውን ነገር መጠቆሙ የዜግነት ሃላፊነት እንጂ እንደቀድሞ ጊዜያት ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች እንደተቃማዊነትና ጠላትነት ተደርገው እንደማይታዩ ተስፋ አደርጋለሁ። ምንአልባትም በሂደት እየጎለበተ በሚሄደው የጊዜው "የመደመር እሳቤ" ውስጥ በአንድ በኩል ጭፍን የሆኑና የኃላፊነት ስሜት የጐደላቸው ትችቶች በሌላው በኩል ደግሞ ማንኛውንም ትችትና ገንቢ አስተያየት መቀበል ሽንፈት/ የበታችነት አድርጐ በመውሰድ የሚፈጠር የጠላትነት ጐራ ከሚቀነሱት ጉዳዮች አብይ ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱልኝ እጠይቃለሁ።

ለዚህች ጽሑፍ የወሰድኩት አርዕስት ከ1960ቹ ጀምሮ እስከ አሁኗ ኢትዮጵያ ድረስ በተደጋጋሚ ነገርግን ለውድቀት ከዳረገን የትምህርት እርምጃ እሳቤ በተለየ መልኩ አዲስ የ ሆነ እይታና ተግባራዊ የሆኑ መሠረታዊ የለውጥ አቅጣጫዎችን በትንሹም ቢሆን ለመፈንጠቅ ነው፡ ፡ አቀራረቤ በተቻለኝ መጠን አንኳር አንኳር የሆኑትን ሃሳቦች በማንሳት አንባቢው በነዚህ እርዳታነት ከህይወቱ ልምዱ ጋር በማዛመድ የግል-ፅብረቃ እንዲያደርግና እንዲሳተፍ ተግባራዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከመጠቆም ባለፈ በዝርዝር አላስቀመጥኳቸውም:: ከዚህም በተጨማሪ ከፅሑፉ አርዕስት አንፃር የጠቀስኩት አዲስ የሆነ እይታ በንድፍ ሃሳብ (theory) አንፃር ከዚህ በፊትም ይሁን በአሁኑ ፍኖተ-ካርታ ከተለመደው ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ (management) አስተሳሰቦች (rationality) በተለየ መልኩ ለትምህርት ጥራት ሲባል ሊከፈል የሚገባ ዋጋ እንዳለ ይጠቁማል።

እንደ ስርዓተ-ትምህርት ቲዎሪስቶች አባባል የትምህርትና ስርዓተ-ትምህርት ጥናቶች (ፍኖተ-ካርታንም ጨምሮ) ታሪክ-አልባ (ahistorical) ናቸዉ ብለዉ ይተቻሉ (Shubert 2008)። ይህ ፅሁፍ በመጀመሪያ እስከአሁን በአገራችን በአግባቡ ያልተጠየቀዉን የትምህርት ፍልስፍና (አሰተሳሰብ) ለመረዳት ይረዳን ዘንድ ጅማሬዉን/ ታሪካዊዉን ዳራ በመዳሰስ በሂደት ድብቅ የተደረገዉን የትምህርት ፍልስፍና እና ማህበራዊ አላማዉን (ማለትም የት አገር፤ በምን ሁኔታ፤ለምን አላማና የማንን ፍላጎት/ interest ለማርካት መፈጠሩን) በገሀድ ያወጣል።

---

* ፒ ኤች ዲ፣ ተባባሪ ፕሮፌሰር፣ ትምህርትና ስነ-ባህርይ ጥናት ኮሌጁ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በመቀጠልም በቴክኒካል ራሽናሊቲ አማካኝነት የተፈጠረዉ በአስተሳሰብና ድርጊት/ ተግባር መካከል መለያየትና የአሁኑን ህብረተሰብ ፍፁምነት ሳይጠየቅ የሚደረግ የትምህርት ማሻሻያ ለምን በተደጋጋሚ ለዉድቀት እንደዳረገን ያስረዳል። በመጨረሻም የአገራችን ትምህርት ጥራትና አግባብነት ዋናዉ ችግር መዋቅራዊ መሆኑን በማሳየት የመፍትሄ አቅጣጫዉም በአስተሳሰብና ድርጊት መሃከል ሁለትዮሽ የሆነ ግንኙነት በመመስረት ለት/ ቤቶችና ለመምህራን ትኩረት በሚሰጥ የትምህርት አስተሳሰብን ያራምዳል።

## ማህበራዊ ውጤታማነት (Social Efficency) እና የሳይንሳዊ አመራር እንቅስቃሴዎች (Scientific Management movements)፡ የ20ኛው ምእተ አመት መጀመሪያ ትምህርታዊ ርዕዮቶች (Ideologies)

ከ1950ዎቹ ከጀመረው የአሜሪካ-ኢትዮጵያ ፖይንት 4 ስምምነት ወዲህ ላለፉት 70 ለሚሆኑ አመታት የኢትዮጵያን ትምህርት የመራው የትምህርት አስተሳሰብ በ20ኛው ምዕተአመት መጀመሪያ በአሜሪካን ሃገር በጊዜዉ ለተከሰተዉ ማህበራዊ ችግር ምላሽ ይሆን ዘንድ የተፈጠረ ነው። በጊዜው የነበረውን ማህበራዊ ችግር እንደ ኮርን ብሌዝ (1990) የተባለች ምሁር አገላለፅ ፍልሰት ከገጠር ወደ ከተማ እና ከሌሎች ሃገሮች በብዛት መከሰቱ፤ የተማሪው ቁጥርና ብዝሃነት መጨመር፤ በጊዜው የነበረው የተለምዶ /traditional ትምህርት በብቃት ተማሪዎችን ለስራ ዝግጁ አለማድረጉ፤ በአጠቃላይ የእውቀት መብዛትና የጋራ የሆነ መግባባት (consensus) መጥፋት ወዘተ እንደሆነ ትገልፃለች። ይህ ከ1780ዎቹ ጀምሮ ‹melting pot› በሚል ስነቃል ሲታወቅ ከ1908 ጀምሮ ግን በብዛት ጥቅም ላይ ሲዉል፤ ከታሪክ አንፃር ግን የተለያዩ ባህልና ቋንቋ ያላቸዉን ማህበረሰቦች ወደ አንድ ባህልና ቋንቋ ህብረተስብ የመለወጥ ሂደት (assimilation) እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ጉዳይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ከጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ጋር በ2001 (እ.ኤ.አ) ባደረጉት ዉይይት ላይ በአሉታዊ ጉኑ ተነስቶ የንጉሱና የደርጉ ዘመን አሰራር እንጂ የአሁኑ የብሄር ‹ዲሞክራሲ› እሳቤ እንደማይወክል ተደርጎ ተወስዶ ነበር።

በዘመኑ የበላይነት በነበረው ቁጥጥር ላይ ያተኮረ ማህበራዊ ሳይንስ እሳቤ መሠረት በጊዜዉ ቅርጽ መያዝ የጀመረውን የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ማህበራዊ አደረጃጀት ትክክለኛነትና በውስጡም ባሉት አባሎቹ (ትምህርትንም ጨምሮ) የሚፈጠሩትን ችግሮች ለማረም ዘገምተኛ በሆነ ጥገናዊ ለውጥ እንጂ አብዮታዊ በሆነ ስር-ነቀል ለውጥን የሚቃወም ነበር። ይህ እሳቤ ማህበራዊ ውጤታማነት (Social Efficency) በመባል ሲታወቅ ለማህበራዊ ችግሩ/ሮቹ በዋናነት አባሉ/ሎቹን ተጠያቂ ሲያደርግ ይህንንም በማሻሻያ/ reform አማካኝነት ይስተካከላል ብሎያምናል። ይህ ወቅት ትላልቅ ኩባንያዎች የአገሪቱን ሀብት ጠቅልለዉ መያዝእና ወደደቡብ አሜሪካ፤ አዉሮፓና አፍሪካ መንሰራፋት የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

በመሆኑም ባህርማዶ በሚያጋጥማቸዉ ጉዳይና በአገር ዉስጥ በካፒታልና ጉልበት መካከል በተፈጠረዉ አለመግባባትና ተከታታይ አመፅን በአግባቡ ከመዳኘት አንፃር አዲስ የሆነ የመንግስት እሳቤ እንዲፈጠር አስችሏል። እንደ ኮርፖሬት ሊበራልስ (corporate liberals) አባባል ከዚህ በፉት ከነበረዉ መንግስት ገበያዉን ለነፃ ገበያውና ለኢኮኖሚዉ ተዋናዮች ይተዉ

(Lassies-faire) ከሚለዉ አቋም ይልቅ የተወሰነ ጣልቃገብነት ሊኖረዉ ይገባል ይላሉ። ነገር ግን የዚህን ጣልቃ ገብነት ባህሪይ በተጨባጭ ሲያስረዱ በሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ማዕቀፍ ዉስጥ ብቻ የሚፈፀም እንደሆነ በጥብቅ ያሳስባሉ።

በዚሁ ጊዜ ሞያዊነትን (professionlization) የተጎናፀፉት የትምህርት አስተዳደር፤ መምህርነትና ስርዓተ-ትምህርት ዉስጥ እነዚህ ትምህርታዊ ርዕዮቶች በግልፅ ይታያሉ። ለምሳሌ ስርዓተ-ትምህርት በአብዛኛው እነዚህን አስተሳሰቦችን እንደቀኖና መቀበሉን እንደ ነቦቢት እና ካርተር የተባሉት የሙያው መስራች በሆኑት ስራዎች ዉስጥ ተንፀባርቀዋል። በጊዜው የአሜሪካ እንደስትሪ በእጅጉ ውጤታማ መሆን እንደቦቢት አባባል የትምህርትና ስርዓተ ትምህርት ዘርፎች አሁን ካለባቸው ችግር ተላቀው ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉት ኢንደስትሪውን የለወጠው የማኔጅመንት (Tyler Management) አሰራር በመቀበል የትምህርትን ብክነትን (Efficiency) መቀነስ ከቻሉ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። Dictionary.com ‹efficient› የሚለዉን ቃል ሲያብራራ "ውጤታማ-በተለይም የስርዓት ወይም ማሽን- ከፍተኛውን ምርታማነት በትንሽ ጥረት ወይም በከፊል ወጪዎች ማግኘት" ይላል:: ይህ የቢዝነስ ቋንቋ ወጪ-ቅነሳ ላይ ያተኮረ ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ት/ ቤቶችን በተጨባጭ ልክ እንደ ‹ትናንሽ ፋብሪካዎች› መወሰዱን እናያለን።

Bobbit (የስርዓተ ትምህርት ቲዎሪ አባትና የነዚህ ርዕዮቶች ዋና አቀንቃኝ) የስርዓተ ትምህርት አስተሳሰብ (theory) ከትምህርት አስተሳሰብ (theory) ጋር ያለዉን ግንኙነት ሲያስረዳ ‹ከህብረተሰቡ ፍላጐት የሚመነጬ እነዚህም ዝርዝር በሆኑ ግቦች (Objectives) እንደሚገለፅና ተማሪው (ግለሰቡ) የሚማረውን ይዘት እንደሚወስኑ ወዘተ ያስረዳል (1918/ 1922) :: Bobbit በተለይ ስለትምህርት አላማ ሲያስረዳ ‹ግለሰቦችን በህብረተሰቡ ውስጥ ላላቸው የተለያዩ ቦታቸው/ሚናዎች ማዘጋጀት› እንደሆነ ይገልፃል (ይህ ሃሳብ በስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ (MoE 2010) ውስጥም በማወቅ ይሁን በስህተት በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልፆአል)።

ይህን የBobbit የትምህርት አላማ በሁለት ዝርዝር ቁም ነገሮች መግለፅ ይቻላል። የመጀመሪያዉና በግልፅ ቋንቋ የተገለፀዉ ‹ትምህርትን እንደማዘጋጃ› (preparation) መወሰዱ (በጊዜዉ የነበረዉን የካፒታሊስት ህብረተሰብ እንደደምብ /norm በመወሰዱ ምክንያት ለወዝአደሩና ለባለሃብቱ ልጆች በማህበረሰቡ ዉስጥ ለሚኖራቸዉ የተለያየ ሚና የሚያዘጋጅ መሆኑ)፤ ሁለተኛዉ ደግሞ ከላይ እንደተገለፀዉ ትምህርት በግለሰብ ሳይሆን በህብረተሰቡ ፍላጎት ላይ የሚመሰረት (አሁን በማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉትን ልዩነቶች እዉቅና የሚሰጥና ግለሰቦችን በማህበረሰቡ ቀድሞ ለተወሰነላቸዉ ሚና ለማድረስ የማህበራዊ ቁጥጥርን አስፈላጊነት ላይ ያተኮረ ፍልስፍና) መሆኑን ነዉ። ከዚህ ቀጥሎ ‹ርዕዮት፤ትርክት፤እዉቀት እና ስርአተ-ትምህርት› ሳይንስ እንደሚለዉ ፍላጎት-አልባ /disinterested ሳይሆኑ እነዚህን የሚያራምዱ ቡድን/ ግለሰብ ፍላጎት ማንፀባረቂያ መሆናቸዉን እነዚህ ርዕዮቶች በተጨባጭ በትምህርቱ ዘርፍ ዉስጥ ያመጡትን አደረጃጀት፤ ተግባርና ራሺናሊቲ መመርመር የግድ ይላል።

በጊዜው የነበረውን ማህበራዊ ሳይንስ አስተሳሰብ ተፅዕኖ (የሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ማህበራዊ አደረጃጀት ትክክለኛነትና የመንግስት ኢኮኖሚያዊ እንጂ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ ዉስን ሚና) የምናየው ይህ ሰው የአሁኑን ህብረተሰብ ፍፁምነት አለመጠየቁ እና ትምህርትንም እንደማዘጋጃ መዉሰዱ በዋናነት (በብቸኝነት) ይህን ኢፍትሀዊ የሆነዉን ህብረተሰብ እንደገና መፍጠሪያ (reproduce) ተደርጎ እንደተወሰደ እናያለን። በተጨማሪ የማናጅመንት አስተሳሰብ በእንደስትሪው ውስጥ እንደፈጠረው አደረጃጀት (ማለትም መሠረታዊ ውሳኔዎችን ‹ፖሊሲ› በማኔጅመንት ሲወሰኑ የፋብሪካው ሰራተኞች ግን በጉልበት ስራው ላይ ብቻ እንዲወሰኑ በማድረግ የካፒታሊስትና የሠራተኞች መደብን) እንደፈጠረ ሁሉ በትምህርት አስተዳደርና በመምህራን መካከል ተመሳሳይ የሆነ ልዩነትና ቁልቁለታዊ የሆነ ግንኙነት (hierarchical relation) ፈጥራል።

ይህ ኢንደስትሪዉን የለወጠዉ አስራር ቀድሞ አእምሮአዊ የነበረዉን ሥራ ወደ ተራ ድግግሞሽ (routines) የተሞላበት አሰልቺ የጉልበት ሥራ መቀየሩ፤ የሠራተኛዉ የስራና የኑሮ ሁኔታዎች እየጎሰቆለ መምጣቱ፤ ተከታታይ የሠራተኛ አመፅ፤ እንዲሁም ከጥራት ይልቅ ቁጥር ላይ ያተኮረ ዉጤት (product) ወዘተ ማስከተሉና እነዚህም ሁሉ አሁን በትምህርቱ ዘርፍ ዉስጥ በስፋት መታየታቸዉ የኢኮኖሚ አስተሳሰብና የፋብሪካ ሞዴል ያመጣዉ መሆኑን እናያለን። የትምህርቱ እሳቤ ዲሞክራሲያን ያገለለ በመሆኑ እስከ አሁን የተሻለ ፍትሃዊና እኩልነት የነገሰባት አገር መገንባት አለመቻላችንን የሚያስረዳን (በተለይ ከ27 አመት የዉሸት ዲሞክራሲ በኃላ አሁን ያለችዉን ኢትዮጵያ ስንታዘብ) እነዚህ ባዶ ተስፋ እንጂ በተጨባጭ በኢኮኖሚያዊ እሳቤ ዉስጥ ሊረጋገጡ የማይችሉ እሴቶች መሆናቸዉ ነዉ።

ይህ አስተሳሰብ ቴክኒካል ራሽናሊቲ (technical rationality) በመባል ሲታወቅ በትምህርቱ ዘርፍም ብዙዎች እንደሚሉት በአስተሳሰብና በድርጊት (theory and practice) መሀከል መለያየትን ፈጥሯል (Apple 1886/ 2004)። ስለዚህም መሠረታዊ የሆኑትን የፖሊሲ፤ ፕሮግራም ወዘተ በማኔጅመንት [በመንግስት/ ትምህርት ሚኒስቴር] ሲወሰኑ ትግበራው ግን በት/ቤቶች እንዲካሄዱ በማድረግ በዚህ ኢኮኖሚያዊ (ኢ-ዲሞክራሲያዊ) እሳቤ የተዋቀረው ሰንሰለታዊ ግንኙነትና ተጠያቂነት (hierarchical relationships and accountability) በት/ቤት ዉስጥ በተጨባጭ የበላይ አካልን ዉሳኔ ለማስፈፀም እንጂ ለመማር-ማስተማር የሚሆን ምቹ የሆነ ሁኔታ አልፈጠረም። ይህን የጋራ መግባባት ሲጠፋ የህብረተሰቡን ፍላጐት በግለሰብ ላይ ለመጫን አስፈላጊ ሆነው የሚታሰቡትን የቁጥጥር እሳቤዎች ልክ እንደመንፈሳዊ ቀኖና በአግባቡ አለመጠየቃቸው ሌሎች አገሮች እያጨዱት ያለውን የትምህርት ውጤት ለማግኘት አልቻልንም።

በትምህርቱ ዘርፍ ዉስጥ ከ1999-2001 ዓ.ም ሲካሄድ የነበረዉ መሠረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ (በእንግሊዝኛዉ Business Process Reengeenering or BPR) የቴክኒካል ራሽናሊቲ የልጅ ልጅ ሲሆን (በ1950ዎቹ ሶሻል ሲስተም ቲዎሪን እናገኛለን) አሁንም ዲሞክራሲን ያገለለ አሰራር

በተጨባጭ ሊያሳካ የማይችለውን ባዶ ተስፋ ይመግበናል። ትምህርት ሚኒስተር (2001ዓ.ም፡ 3) ‹የጥናቱን አጠቃላይ ፍልስፍና ወይም የጥናቱ ራዕይ› በሚል ሲጠቅስ ‹የትምህርትና ሥልጠና ሥርአቱ ለሀገሪቱ ልማት አስተዋጽዖ በሚያደርግ፤ የትምህርት ብክነትን በሚያስወግድ፤ በብቃት የተማረና በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ዜጋ ሊያፈራ በሚችልና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ የሚካሄድበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ነዉ› ይላል።

ብዙውን ጊዜ ኢኮኖሚያዊ/ማናጀሪያል የሆነው አሰራር ከሚተችበት ሰንሰለታዊ ግንኙነት፤ የቁጥጥር ባህልና ቀላል/ ቀጥተኛ የሆነ (simplistic/ linear) አካሄድ፤ እንደ Fullan and Beyer (1988) አባባል "ከቁምነገሩ (Substance) ይልቅ ብክነት-አልባነት (Effiency) ላይ ለተመሰረተ ቀደም-ተከተል (Procedures) ትኩረት መስጠቱ" አሁን ላለንበት ሁኔታ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡ ፡ Dictionary.com -procedures የሚለዉን ሲገልፅ "አንድ ነገር ለመስራት የሚያስችል አንድ ወይም ኦፊሴላዊ መንገድን" መከተል ይላል። የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እና ፍኖተ-ካርታ ጥናት መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎችን (ለምሳሌ በኢትዮጵያ ደረጃ ትምህርት፤አስተማሪ፤ተማሪ ማለት ምን እንደሆነ? የትምህርት ቤቶች ሚና ምንድነዉ ወዘተ) ከመጠየቅ በዚህ ዙሪያ ከማሰብና ኢትዮጵያዊ የሆነ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በአንድ ታሪካዊ ወቅት በአሜሪካን አገር ዉስን/specific ለሆነ ማህበራዊ ችግርና አላማ ተብሎ የተፈጠረን ዘይቤ እንደአለም-አቀፋዊ/ universal ሁኔታ ቆጥረን የነርሱን መመሪያ/ procedures ብቻ መከተላችንና በተደጋጋሚ መክሰራችን በትምህርት ታሪካችን ዉስጥ በደማቅ ቃል ተፅፎ ይገኛል።

## የትምህርት ማሻሻያዎች ችግር የመንደርደሪያ ሀሳብ

Fullan and Hargreaves (1998) የሚባሉ በትምህርት ቤትና በማስተማር ባህል ላይ እንዲሁም የለውጥ ሂደት አስቻጋሪነት ላይ በብዛት ያጠኑ ምሁራን "What's worth fighting in your school?" በሚለው መፅሐፋቸው አንድ መሠረታዊ የሆነ የመነሻ ሃሳብ ግልፅ በማድረግ ይጀምራሉ:: ይኸውም "የትምህርት ማሻሻያ በየጊዜው ቢደረግም በተደጋጋሚ አልተሳካም" (3):: በእኛም ሀገር ምንም እንኳን የጋራ የሆነ እውቅና ባይሰጠውም በዚህ ፅሑፍ መግቢያ ላይ እንደጠቀስኩት ከ1960ቹ (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ያካሄድናቸው የትምህርት ማሻሻያዎች እስከ ቅርቡ በ2008 (እ.ኤ.አ) የትምህርት ጥራት ፖኬጅ (ትግበራው እስከ አሁኗ ሰዓት ዘልቋል) ድረስ ውጤቱ የቀደመውን ማሻሻያ ውድቀቶችን በአዲስ ማሻሻያና አዲስ ተስፋ እየተካን እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ አለን።

ይህንን በሶስቱም የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ (በንጉሱ፣ በወታደራዊ፣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ) በተደጋጋሚ ሃትሪክ የሰራንን እንደ የተለመደ ሁኔታ እንጂ እንደ ችግር ቆጥረነው መፍትሄ ፍለጋ አልጀመርንም:: ከዚህ በተቃራኒዉ፤ ፉላንና ሃርግሬቭስ ግን ይህንን ተደጋጋሚ ውድቀት ሲያስረዱ "በእኛ እምነት"ይህ የሆነበት ምክንያት "ማሻሻያው ምንአልባት መምህራንን ረስቷል ወይንም ደግሞ ማስተማር ማለት በአጠቃላይ ምን ማለት እንደሆነ ከሚገባው በላይ አቅልሎታል" ይላሉ:: የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና የአሁኑ ፍኖተ-ካርታ ማሻሻያዎች በመሠረቱ አንድ አይነት

አስተሳሰብ (Theory) የሚያራምዱ መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል፡ ፡ሁለቱም የሚነሱት ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ (Society) ፍላጐቶችና ከአገራዊ (National) ድባብ (Context) ሲሆን እነዚህ ፍላጐቶች የትምህርቱ ዘርፍ አላማ በመሆን የትምህርቱን አደረጃጀት፤ ስርዓት ትምህርቱን፤ ግምገማና ምዘናውን ወዘተ ይወስናሉ፡፡

የትምህርቱ አላማና ይዘቱ ወዘተ በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት (ፖለቲከኞች እና የት/ሚኒስቴር የበላይ ሹሞች) የሚወሰን ሲሆን ከክልል ት/ቢሮ እስከ ወረዳ ት/ጽ/ቤቶች ድረስ በተቆጣጣሪነትና፤ ት/ቤቶች ደግሞ በተግባሪነት መዋቀራቸውን ቀድሞ ያነሳነውን የኢንድስትሪ እሳቤ (በአስተሳሰብና በተግባር መካከል ያለውን መለያየትና እና በወጪ መቆጠብ (Efficiency) ፊት-አውራሪነት መደራጀቱን በተግባር እናያለን፡፡ ይህ አስተሳሰብ ትኩረቱ በላይኛው እርከን (National gov't/ society/MoE) የተደነገጉትን አላማዎች፤ ይዘቶችና ዘዴዎች የበታችኛው እርከን (ት/ቤት፣ የወረዳ መንግስትና የአካባቢ ማህበረሰብ) እንደሚፈፅም ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ት/ቤቶችና መምህራንን በቀጥታ ትኩረት ከማግኘት ይልቅ ይህንን በተዘዋዋሪ አገራዊ አላማን ከማሳካት አንፃር ብቻ (Efficiency) ስለሚያያቸው እንደ ምሁሮቹ አባባል «የተረሱ» ያደረጋቸዋል፡፡

በዚህ ቴክኒካል ራሺናሊቲ አስተሳሰብ መሠረት መምህራን በተግባር የሚወሰዱት እንደ ቴክኒሺያን (በቅርቡም በቢዝነስ ፕሮሰስ ሪኢንጅነሪንግ BPR-መሠረት «ፈፃሚ») ማለትም በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት የሚተገብሩ እንጂ እንደባለሞያ/ professional የሚያስቡ (thinker) እና የሚወስኑ (decision-maker) እድርጐ አይወስዳቸውም፡፡ እንደዚሁም በዚሁ እሳቤ ማስተማር ደግሞ ቀላል የቴክኒክ ሥራ (technical activity)- አንድ ኦፊሴላዊ መንገድን/ መመሪያ ተከትሎ የሚሰራ (ለምሳሌ- ትምህርቱን ማስተዋወቅ- ዋናዉን ይዘት ማስተማር በመጨረሻም መከለስ-አንድ አይነት አሰልቺ ሂደት) ተደርጐ ይወስደዋል፡፡ መምህራን በትምህርት አላማና ይዘት (በማኔጅመንት የሚወስኑ) ይልቅ በማስተማር ዘዴው ላይ ብቻ (በበላይ አካላት የተወሰኑትን ከማስፈፀም አንፃር) ስለሆነ ያላቸው መብት (mandate) ተብሎ ስለሚታሰብ የቅድመሙያና የተከታታይ ሙያ ማሻሻያዎች (የድህረሙያ) እንደ «ሥልጠናዎች» (እንጂ የመምህራን ትምህርት/ education ተብሎ ብዙ ጊዜ አይጠራም) መምህራንን የተለያዩ ቴክኒካዊ ክህሎቶች እንዲያገኙ ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ ይህም በአጠቃላይ የሚያሳየን በቲዎሪም ይሁን በተግባርም ማስተማር ቴክኒካዊ ተደርጎ መወሰዱን ነዉ፡፡ስለዚህም በመንግስት ከስርዓተ ትምህርቱ ከተቀመጠው አላማ (እና ይዘት) ውጪ እንደባለሞያ የአካባቢማህበረሰብ በትምህርት ሊያራምድ የሚችለውን አላማ እንዳያሳኩ ይከለክላሉ፡፡

ዋናው የትምህርት ጥራትና አግባብነት ችግር መዋቅራዊ መሆኑን በተዘዋዋሪ መንገድ ሲገልፁ ማሻሻያዎች ያልተሳኩበት ምክንያት ትኩረታቸው በመላው ት/ቤት (Total School) እና በመላው መምህር (Total Teacher) ላይ ባለማድረጉ እንደሆነና የነዚህን ትኩረት-አልባ አካሄዶች ድምር ዉጤት ደግሞ «ከተማሪዎች መማር ጋር ይገናኛል» ይሉናል፡፡ ትምህርት

ማህበራዊ ተግባር (social practice) መሆኑን በተማሪውና መምህሩ መካከል ግንኙነት መኖሩን-ማለትም የተማሪው መማር በመምህሩ መማር ላይ የተመሠረተ መሆኑና በተራዉ የመምህሩ መማር በማሻሻያዎቹ ገዥ አስተሳሰብ ምክንያት ሊሳካ አለመቻሉን መዋቅራዊ በሆነ ትንተና ከመስጠት ይልቅ በፍኖተ-ካርታዉ የተጠቀሱትን አይነት የፍጥነት ማስተካከያ (quick fix) ውስንነት ሲገልፁ ‹በፍጥነት የሚደረግ ማስተካከያ የለም። ነገር ግን ፈጣን የሆኑ ውድቀቶች ግን አለ ይሉናል።

## ይህንን ሁኔታ እንዴት ማስተካከል እንችላለን?

ስለዚህ አሁን ለት/ቤቶችና ለመምህራን ትኩረት እንደሚሰጥ ማሻሻያ አድርገን ስንቃኝ ‘አንድ ኦፊሴላዊ መንገድን/ መመሪያን ተከትሎ በፍጥነት ከሚሰጥ ማስተካከያዎች ይልቅ በዋናነት ሊነሳ/ ሲጠቀስ የሚገባው በተማሪዎች መማር ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ ከሚችሉ በት/ቤትና በመምህራን ዙሪያ ምን አይነት ሁኔታዎች (Conditions)፤ እሴቶች (values) እና አሠራሮች ያስፈልጉናል? የሚለዉ ነዉ።ይኸውም በዋናነት ወጪ-ቆጣቢነት (efficiency) በሆነው የኢንደስትሪ እሳቤ መሠረት የተዋቀረው በትምህርት ቤቶች በተጨባጭ የፈጠረው ሁኔታዎች (conditions): አሠራሮች (routines): የመምህርና ማስተማር እሳቤዎች/ትርጉም ድምር ውጤት ተራማጅ ለሆኑ አስተሳሰቦች (ተማሪ-ተኮር ማስተማር ዘዴ፣ብዝሃ ባህል ትምህርት (multicultural; multiple intelegence፣ constructive teaching and learning ወዘተ) ሊያስተናግዱ አለመቻላቸው ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ትኩረታችን በአገራዊ (የኢትዮጵያ ህብረተሰብ) እና መንግስት/ ትምህርት ሚኒስቴር አላማ፤ እስትራቴጂ እና ፕሮግራም ላይ በመሆኑ የክፍል ወስጥ ህይወት ማለትም እውቀት በተጨባጭ ማለት ከባለስልጣን፣ከመጽሐፍት እና ከመምህራን የሚመነጭ ነገር ግን በተማሪዎች የማይጠየቅ ተደርጐ እንዲወሰድ፤ ማስተማር ማለት ደግሞ ይህንኑ ግዑዝ እቃ መምህራን ከመጽሐፍ ‘ማስተላለፍ ‘እንዲሁም መማር ማለት ይህንን ግዑዝ እቃ እንደ ‘መቀበል/ መሸምደድ ተደርጐ በተግባር እንዲወሰድ አድርጓል።

ስለዚህም ይህን ኦብጀክቲቭ (objective) የሆነውን እውቀት ማስተማር (መማር) የሚቻለው ት/ቤቶችና ክፍሎቻቸዉ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል በሚለው ግንዛቤ መሠረት የቁጥጥር ስርዓት ለመማር ማስተማር እንደአስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች (conditions) ተደርገው እንዲወሰዱ አድርጓል። እዚህ ላይ ይህንን የት/ቤትና የክፍል ውስጥ ህይወት ለጊዜው ወደጐን ትተን እንዴት ልንቀይረው እንደምንችል ቅድም ወዳነሳነው ጥያቄ እንመለስ ;;የተማሪዎችን መማር የሚደግፍ የመምህርነት እሳቤ እና የት/ቤት ሁኔታዎች (conditions) ሌሎች የተሻለ የት/ሥርዓት ካላቸው አገሮች ልምድ አንፃር እንደሚያሳየው “ትክክለኛ የሆኑ ነገሮች” (right things) እንደፉላንና ሃርግሬቭስ አባባል “መሠረታዊው የስራ ሁኔታ (work condition) እና በመምህራን ህይወት ውስጥ ስር የሰደዱ እንደሆኑና (ቅድም በቴክኒካል ራሺናሊቲ የተሸረሸሩ ሁኔታዎች ናቸዉ) እነዚህ ደግሞ በተራቸው የተማሪዎችን መማር ላይ ተፅዕኖ ያደርጋሉ” ይሉናል። ከዚያም በመቀጠል ተማሪዎቻችንን ለማሻሻል ብቸኛው ቁልፍ ነገር መምህራንንና ት/

ቤቶችን ማሻሻል ነው። ለመምህራኖቻችን የሚደረገው ተገቢ የሆነ ድጋፍና የተማሪዎችን ስኬት ለማረጋገጥ መምህራንና ተማሪዎች በተመሳሳይ ከፍ ያለ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ይሉናል።

በተጨባጭ ግን ይሄ ለመምህራንና ተማሪዎች መሠጠት ያለበት ትኩረት ምንድነው? ቅድም እንደተጠቀሰው መሠረታዊ የሆነው ጥራት አልባው የትምህርት ማሻሻል ችግር መዋቅራዊ እንደሆነና በትምህርቱ ሥርዓት ውስጥ ያለው የኃይል አሰላለፍ በናሽናል ደረጃ ያሉትን ፖለቲከኞችንና የትምህርት ኃላፊዎችን ውሳኔ ከማስፈፀም ባለፈ የትምህርት ጥራትን ማስተናገድ ባለመቻሉ እንደሆነ ይህም ሊስተካከል የሚችለው ከቴክኒካል ራሺናሊቲ በተፃራሪ ለት/ቤቶችና ለመምህራን ትኩረት በሚሰጥ አስተሳሰብ ስንተካ ነው። ከዚህ አንፃር የፍኖተ-ካርታዉ ጥናት ያነሳው ነገርአ ለመኖሩና በዋናነትም ይህን ቴክኒካል ራሺናሊቲ ባለመጠየቁ በእኔ እምነት የትምህርትና ስልጠናው ፖሊሲ ያስገኘልን ዘርፈ ብዙ ውድቀቶችን ከማስቀጠል ባለፈ መፍትሄ ሊሆን አይችልም።

ከዚህ አንፃር Fullan and Hargreaves (1998፡3) አዲስ የሆነ የመምህርነት እሳቤና ከዚህ አንፃር ሊደረጉ ስለሚገባቸው መዋቅራዊ ለውጦች በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያስረዱ "አዲሱን ምእተ-አመት እየቀረብን ባለንበት በዚህ ወቅት፤ ለትምህርት ቤቶች፣ ለመምህራንና መሪዎቻቸው አስቸጋሪው ነገር በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ መስተጋብራዊ ሞያዊነት (interactive professionalism) የመገንባት አስቸጋሪነት ነው" ይላሉ። በዝርዝር ይህንን አዲስ የመምህርነት እሳቤና ከዚህ አንፃር በትምህርትቤት ውስጥ ሊኖሩ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች (conditions) በተመለከተ ሲያስረዱ በመስተጋብራዊ ሞያዊነት ውስጥ 1) መምህራን እንደ ቡድን በደንብ በሚያውቋቸው ልጆች ፈንታ ወይም አብረዋቸው ውሳኔ እንዲወስኑ የሚያስችል ትርጉም ያለው የመወሰን ስልጣን ተፈቅዶላቸዋል፤ 2) መምህራን እነዚህን ውሳኔዎች ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን እርዳታና ድጋፍ ባለበት የትብብር ባህል ውስጥ ያደርጋሉ፤ 3) የመምህራን የጋራ ውሳኔዎች ግብኣቶች፣ሃሳቦችንና ሌሎች ወዲያውኑ ተግባራዊ የሚደረጉ ነገሮችን ከመካፈል ባለፈ መልኩ መምህራን በሚያስተምሩት ይዘት፣ ስነዘዴ፣ አላማእናእሴት (values) ላይ ጥልቅ የሆነ ጽብረቅ (critical- refelection) ያደርጋሉ፤ 4) መምህራኖች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ላለው ተከታታይ መሻሻል ደንቦች (norms) ቁርጠኝነት አላቸው፤ 5) የክፍል በሮቻቸውን ከፍት አድርገው በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እና ውጪ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ሲወያዩ፣ ሲያደርጉ (action) እና ሥራዎቻቸውን ሲገመግሙ መምህራን በመሠረቱ ይበልጥ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ይህንን አዲሱን የመምህርነት እሳቤ እና ተያያዥ የሆኑ አደረጃጀቶችና አሠራሮች ቴክኒካል ራሺናሊቲ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ ነው በሚባል መልኩ የትመህርቱን ባህርይ ሊቀይር ይችላል። በዚህም ምክንያት 1) መምህራን ፈፃሚ ብቻ ሳይሆኑ አሳቢ እና ውሳኔ ሰጭ መሆናቸውን፤ 2) የእርስ በርስ ትብብር ባህል እንዲፈጠር (collaborative culture) እና ለሞያተኞች እድገት አስተዋጽኦ ማድረጉ፤ 3) በትምህርት ቤቱ ካለ ይዘትና አላማ ባለፈ የትምህርትን ማህበራዊ እሴት ሁሉ

የሚጠይቁ ባለ ሙያዎች መሆናቸዉ፤ 4) እንደባለሙያ ሁልጊዜ ሞያቸውን የሚያሻሽሉ እና 5) እንደ ዲሞክራሲያዊ ተጠያቂነት ለአካባቢያቸው ማህበረሰብ እና ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በኩል ሩቅ ለሆነው ብዙም ግልፅ ያልሆነው አገራዊ ድባብ (ወይም ቁልቁለታዊ ተጠያቂነት) በማስተካከል ት/ቤት ለአካባቢያቸውአግባብ-የሆነ (relevant) ትምህርት እንዲያረጋግጡ ይረዳሉ። አገራዊ እድገት የአካባቢዎች እድገት ድምር ውጤት በመሆኑ ብዝሃነትን በአንድነት ሊያረጋገጥ የሚያስችል ነዉ።

በመጨረሻም በትምህርት ቤትና መምህር ላይ ትኩረት በማድረግ ቀጥለው ሲያስረዱ "የመስተጋብራዊ ሙያዊነት ችግር የት/ቤት ተከታታይ መሻሻል ችግር ነው። ይህ ሂደት በተራው የተማሪዎች ውጤት እንንዲሻሻል ያግዘናል" ይሉናል:: ከዚም ይህን ፁሑፋቸውን ለጊዜው ሲያጠቃልሉ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥም ይሁን ከእነርሱ ጋር የሚሰሩ ማንም ይሁን ማን ይህንን ችግር አይዘነጋ: :የት/ ዘርፍ የበላይ መሪዎች የትምህርት ቤቶችና የመምህራንን ተነሳሽነት ከመደገፍ ባለፈ እንዳያደናቅፉ በመጠቆም ይሄ ችግር ሁላችንንም በጋራ የሚመለከት ጉዳይ ነው አሁን በአብዛኛው የሚታየው ርህራሄ ስሜት አልባ (unsympathetic) እና ድጋፍ አልባ (unsupportive) የስራ አካባቢ ቢሆንም ይህ ጉዳይ አዎንታዊ የሆነ ድርጊት እንድናደርግ ይጠይቀናል። ይህንን የጠለቀ ዲሞክራታይዘሽን ለትምህርት ጥራት የሚከፈል «ዋጋ» አድርጌ አቀርባለሁ።ቁርጠኝነት ከመንግሰትና ከትምህርት ኃላፊዎች በብርቱ ይጠበቃል።

## ዋቢ መድሐፍት


Akalewold Eshete (2016). The Nature of Curriculum Practices in Primary Education: An Invitation to Curriculum Theorization in the Ethiopian Context. Unpublished PhD Dissertation, Addis Ababa University School of Graduate Studies.

Akalewold Eshete (2018). What would be the Price of Quality Education. Fe-Te-He Megazine Year 1, No 08, Tahisas 2011 ET.

Corhbleth C. (1990) Curriculum in Context. UK The Falmer Press.

Beyer L and Apple M (1988). Values and Politics in the Curriculum. In Beyer L E and Apple M W (Eds) The Curriculum: Problems, Politics and Possibilities. Albany: State University of New York Press.

Bobbitt F (1918/ 2004). Scientific Method in Curriculum Making In Flanders D J and Thornton S T (Eds) TheCurriculum Studies Reader, New York: Routledge Falmer.

Fullan M and Hargreaves A (1998). What's Worth Fighting for in Your School? London: Open University Press.

ትምህርትሚኒስተር (2001 EC). የተማሪዎችና የሠልጣኞች ልማት አንካር የሥራ ሂደት (Students and trainees Development Core Work Process) (Unpublished Document)

Schubert W (2008). Curriculum Inquiry.In Connelly, M; He, M F and Philion, J (Eds) The sage Handbook of Curriculum and Instruction. Los Angeles: Sage Publication.

Apple M (1986/ 2004). Controlling the Work of Teacher, in Flinders D. J and Thornton S. J (eds) The Curriculum Studies Reader (2nd ed). New York: RoutledgeFalmer

MOE (2010). Curriculum Framework for Ethiopian Education KG- Grade 12. Addis Ababa: A. M Printing & Packaging P.L.C.